# የጉዞ መዝሙር

## 1. ተናገሩ

ተናገሩ ድንቅ ሥራውንም መስክሩ/2/
ተአምሩን ለዓለም ንገሩ/2/
ድንቅ ሥራውን መስክሩ

## 2. ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብሔር/2/ ምስጋና ይገባሃል/2/
ለዚች ዕለት ለዚች ሰዓት በሰላም
በጤና አደረስከን

## 3. እስመ አልብነ ረዳኢ

እስመ አልብነ ረዳኢ በጊዜ ምንዳቤ ወኃዘን/2/
እስመ ዘእንበሌከ ባዕደ ኢነአምር/4/
ትርጉም፣ በችግርና በሐዘን ጊዜ የሚረዳን የለም እኛ ከአንተ በቀር ሌላ አናውቅምና

## 4. ረድቶኛል እና እግዚአብሔር ይመስገን

በወጀብ በዐውሎ ውስጥ በመከራዬ ቀን/2/
ረድቶኛልና እግዚአብሔር ይመስገን
አድኖኛልና እግዚአብሔር ይመስገን

## 7. ኵሎ ዘፈቀደ

ኵሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር/2/
በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ ወበኵሉ ቀላያት/4/ /2/
ትርጉም:- እግዚአብሔር በሰማይና በምድር በባሕርም በፈሳሾችም ሁሉ የወደደውን አደረገ

## 8. ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው/2/
መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/2/
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/
እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/2/
በትጋት ተራምደን እንግባ በጠዋት/2/
በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት/2/
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/
የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/
ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት/2/

## 9. ኖላዊ ትጉህ

ኖላዊ ትጉኅ ዘኢትነውም/2/
ማኅበረነ/2/ ዕቀብ በሠላም/4/
የማታንቀላፋ ተጉሀ እረኛችን/2/
ጠብቅልን በሰላም ማኅበራችንን/4/

## 10. ነአምን በአብ

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ በወልድ/2/
ወነአምን/4/ ነአምን በመንፈስ ቅዱስ/2/
እናምናለን በአብ እንምናለን በወልድ/2/ /2/
እናምናለን/5/ በመንፈስ ቅዱስ/2/

## 11. እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው

እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው/2/
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማን ነው/2/ } 2
አምላኬ መመኪያዬ ነው

## 12. መድኃኔዓለም አዳነን

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ/2/
ደስ ይበለን/2/ እልል በሉ/2/አዳነን በማይሻር ቃሉ/2/

## 13. አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነተህ አመሰግንሃለሁ እልል/2/
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም/2/

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ
አዝ
አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ
አዝ
ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ሥጦታ

በቀንም በሌሊትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባሕርይህ ዕጹብ ለአንተ ሥራ

አዝ

አምላክ ሆይ ምስጋና  ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል  ሳይጎድል እንደገና

## *14.* <u>አማን በአማን</u>

አማን በአማን/4/
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም/4/
<u>ትርጉም</u>፣ እውነት በእውነት የሥላሴ መንግሥት ዘለዓለማዊ ነው።

## *15.* <u>ንሴብሖ</u>

ንሴብሖ/2/ ለእግዚአብሔር/2/
ስቡሓ ዘተሰብሓ/4/
እናመስግነው/2/ እግዚአብሔርን/2/
ምስጉን ነው የተመሰገነ/4/

## 16. <u>ኃይል የእግዚአብሔር ነው</u>

ኃይል የእግዚአብሔር ነው
ማዳን የእግዚአብሔር ጥበብ የእግዚአብሔር} 2
አንመካም በጉልበታችን
እግዚአብሔር ነው የኛ ኃይላችን} 2

## 17. <u>ንሰሐ እንግባ</u>

ንሰሐ እንግባ ኃጢአት መሥራት ይቅር/2/
የአምላክ ባለሟሎች እንሁን በምግባር
የአምላክ ባለሟሎች እንሁን} 2

## 18. <u>ኢትዮጲያ ታበጽህ እደዊሃ</u>

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ኃበ እግዚአብሔር/2/
እንዘትብል <u>አምላኪዬ</u>/2/ ነጽረኒ ወአድኅነኒ
እምኃይለ ጸላኢ ወፀር} 2

*<u>ትርጉም፣ በምሕረት ዓይን ተመልከተን ከጠላት ኃይል አድነን እያለች ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረለች</u>*

## 19. <u>ያከበርዋ ለሰንበት</u>

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት
ጻድቃን በውስተ ገነት } 2

ወኵሉ ፍጥረት ዓሣት ወአናብርት
እለ ውስተ ደይን ያዕረፉ ባቲ
እስመባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ } 2

ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት
ጻድቃንም በገነት } 2

ፍጥረታት በሙሉ ዓሣዎችና አንበሪዎች
በመቃብር ያሉ ያከብሯታል
አምላክ በእርሷ እንዳረፈ ከሥራው ሁሉ } 2

## 20. <u>ያከበርዋ ለሰንበት</u>

ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሰማያት
ጻድቃን በውስተ ገነት } 2

ወኵሉ ፍጥረት ዓሣት ወአናብርት
እለ ውስተ ደይን ያዕረፉ ባቲ
እስመባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ } 2

ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት
ጻድቃንም በገነት } 2

ፍጥረታት በሙሉ ዓሣዎችና አንበሪዎች
በመቃብር ያሉ ያከብሯታል
አምላክ በእርሷ እንዳረፈ ከሥራው ሁሉ } 2

## 21. <u>እንተ በምድር</u>

እንተ በምድር ሥረዊሃ ወበሰማይ አዕፁቂሃ/2/
ሐረገ ወይን/2/ ድንግል ሐረገ ወይን/2/
<u>ትርጉም</u>:– እመቤታችን ሥሯ በምድር
ቅርንጫፏ በሰማይ የሆነ የወይን ሐረግ ናት

## 22. <u>ይዌድስዋ</u>

ይዌድስዋ <u>መላእክት</u>/2/ለማርያም /2/
በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ
በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ } 2
<u>ትርጉም</u>:–በመጋረጃ ውስጥ መላእክት
ማርያምን ያመሰግኗታል ሰላምታ ይገባሻል
ማርያም አዲስቷ እንቦሳ ይሏታል።

## 23. <u>ሰአሊለነ ቅድስት</u>

ሰአሊለነ ቅድስት እንልሻለን/2/
እንደ ኤፍሬም እንደአባታችን } 2
ለምኝልን እመቤታችን

ተስፋቸው ነሽና ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከዘላለም
ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው } 2
በአንቺ ጸሎት ጻነች ሕይወታቸው
አዝ

ስምሽም ሥልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃልኪዳን ገባልሽ ዓለሙን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ } 2
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ
አዝ

ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትዝል ሲከብዳት ኃጢአት
ጨልሞብን ግራ ሲገባን } 2
ብርሃናችን ነይ እናታችን
አዝ

የልባችን ኀዘን እጅጉን ከብዶናል
ኃጢአታችን በዝቶ መቆም ተስኖናል
አንደ ኤልሳቤጥ አንደዘመድሽ } 2
ደስ አሰኘን ይሰማ ድምፅሽ
አዝ

## 24. <u>ኢያቄም ወሐና</u>

ኢያቄም ወሐና እናት አባትሽ
ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስዕለት የሰጡሽ } 2
መና ከሰማያት የወረደልሽ
ፍጹም ድንግል የሆንሽ ማርያም አንቺ ነሽ
አ/4/ እመ ክርስቶስ ማርያም አንቺ ነሽ/2/

## 25. <u>ማኀደረ መለኮት</u>

ማኀደረ መለኮት/2/
ማርያም እመብዙኃን/4/
<u>ትርጉም</u>:- የመለኮት ማደሪያ የሆንሽ
እመቤታችን ማርያም የብዙኃን እናት ነሽ

## 26. <u>እመቤታችን ማርያም</u>

እመቤታችን ማርያም ማኅበራችንን  
ጠብቂልን በምልጃሽ } 2  
ከመናፍቃን ከከሃድያን ከጠላት ሰይጣን  
ሰውረሽ እንድትጠብቂን በምልጃሽ } 2

## 27. <u>ማርያም ኃዘነ ልቦና</u>

ማርያም ኃዘነ ልቡና ታቀልል/2/  
ኃዘነ ልቦና/4/ ታቀልል/2/  
ማርያም የልብን ኃዘን ታቀላለች/2/  
የልብን ኃዘን/4/ ታቀላለች/2/

## 28. <u>እመቤታችን ለአንቺ</u>

እመቤታችን ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል/2/  
ከሴቶች ሁሉ/3/ ተመርጠሻል  
ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል  
ተበሰረላት/3/ የመመረጥ ክብር  
አዝ  
እያረጓጓት የሰማይ መላእክት/2/  
ቤተመቅደስ ኖረች/3/ አሥራ ሁለት ዓመት  
አዝ  
መንፈስ ቅዱስም እንደቀረባት አውቆ/2/  
ሰገዳላት/3/ ዘካርያስ ታጥቆ

## 29. <u>ልዑል ውእቱ</u>

ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር/4/  
ሚካኤል/2/ ልዑለ መንበር/2/  
<u>ትርጉም</u>:– ከፍ ከፍ ያለነው መቀመጫውም ከፍ ከፍ ያለነው ሚካኤል መቀመጫው ከፍ ከፍ ያለነው

## 30. <u>ልዑል ውእቱ</u>

ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር/4/  
ሚካኤል/2/ ልዑለ መንበር/2/  
<u>ትርጉም</u>:– ከፍ ከፍ ያለነው መቀመጫውም ከፍ ከፍ ያለነው ሚካኤል መቀመጫው ከፍ ከፍ ያለነው

## 31. <u>መልአከ ሰላምነ</u>

መልአከ ሰላምነ ሊቀመላእክት ዑራኤል/2/
ሰአል ወጸልይ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም } 2

<u>ትርጉም</u>:- የሰላም መልአክ ቅዱስ ዑራኤል
ስለ እኛ ለምንልን ጸሎታችንንም
በመድኃኔዓለም ፊት አሳርግልን

## 32. <u>እልፍ አእላፋት</u>

እልፍ አእላፋት ወትእልፊት
ቅዱሳን ንጹሐን መላእክት
ቆሙ ለአገልግሎት ፀንተው በአንድነት
ቅዱስ/3/ አምላክ በማለት
ኢዮር ራማ ኤረር የመላእክት አገር
የሃይማኖት የፍቅር የእምነት ምስክር
እውነት የታየብሽ የመላእክት ክብር
አዝ፣.....
እንጽና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግማሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ
አዝ፣.....
የሳጥናኤል ምኞት እንደአበባ ረግፎ
ሚካኤል ተሾመ በእምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ ጸጋውን ተገፎ
አዝ፣....
ቅዱሳን መላእክት በእምነት የጸናችሁ
በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ
ስግደት ዘበጸጋ እንስገድላችሁ

## 33. <u>ጊዮርጊስ ኃያል</u>

ጊዮርጊስ <u>ኃያል</u>/2/ መስተጋድል/2/
ገባሬ ተአምር/2/ ኮከበ ክብር/4/
<u>ትርጉም</u>:- ጊዮርጊስ አርበኛ ኃይለኛ ተጋዳይ ነው አስደናቂ ተአምር የሚሠራ ተጋዳይ ነው

## 34. <u>ገብረ መንፈስ ቅዱስ</u>

ገብረመንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን ናቸው/2/
ይኸው ለዘላለም ያበራል ሥራቸው/2/

## 35. <u>ተክለሃይማኖት</u>

ተክለሃይማኖት የዓለም ብርሃን ናቸው/2/
ይኸው ለዘላለም ያበራል ሥራቸው/2/

## 36. <u>ጼና አልባሲሁ</u>

ጼና አልባሲሁ/2/ ለገብረ መንፈስ ቅዱስ
ከመጼና ስሒን } 2
አልባሲሁ ዘሜላት/2/ ዘወረደ ውስተገነት/2/
<u>ትርጉም</u>:- የገብረመንፈስ ቅዱስ ልብሳቸው
ከገነት እንደ ወረደ ነጭ ሐር ነው

## 37. <u>አባ አቡነ</u>

አባ አቡነ/2/ መምህርነ አባተክለሃይማኖት/2/
እምአእላፍ ኅሩይ/2/ <u>አባ</u>/6/ አቡነ ተክለሃይማኖት/2/
<u>ትርጉም</u>:- መምህራችን አባ ተክለሃይማኖት
ከብዙዎቹ መካከል የተመረጥክ ነህ

## 38. <u>ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ</u>

ለተክለሃይማኖት ጻድቅ መጠነ በዝኃ ሕማሙ/2/
ትዌድሶ ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ/4/
እስመ በውስቴታ ተገብረ ፍለሰተ ሥጋሁ ወአፅሙ/2/
አዝ.......
እምነ አድባራት ኩሎን ዘተለዓለት በስሙ/2/
አዝ......
ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ/2/
አዝ......
<u>ትርጉም</u>:- ጻዱቁ ተክለሃይማኖት ብዙ ሕማም የተቀበለባት የሥጋውና የአፅሙ ፍልሰት የተደረገባት በስሙ ከተሰየሙ አድባራት በላይ የሆነች ኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የቀደሳት ደብረሊባኖስ ተክለሃይማኖትን ታመሰግናለች

## 39. <u>እንዘ ተሐቅፊዮ</u>

**/ፋንቱ ወልዴ - ቁ.4/**

እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ <u>ድንግል</u>/2/ /2/
ምስለ ሚካኤል/4/ አ ሱሕ ወገብርኤል/2/ <u>እ□</u>/3/
<u>ትርጉም</u>:- ድንግል ሆይ ሕፃንሽን /ልጅሽን/ ታቅፈሽ ደስ ካለው ከሚካኤል እና
□ስታን ከሚያበስር ከገብርኤል ጋር ነይ::

## 40. አንቺ የወይን ሐረግ

/መሪ. ዮሐንስ ስመኝ - ቁ.1/

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ/2/
ምግብ ሆኖ/2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለኛ ቤ□/2/ ኧ□
ባንቺ ሰማይነት የወጣው ፀሐይ/2/
ብርሃን ነው/2/ ለፃድቃን ስሙም አዶናይ/2/ ኧ□
አዝ...
ኘ□ል ትመስያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ/2/
ለመላእክት/2/ የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ/2/ ኧ□
አዝ...
የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኰከብ መገኛ/2/
በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለኛ/2/ ኧ□
አዝ...

## 41. ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንዒ ሠናይትየ ማር□ም/2/
ንዒ ድንግል ንዒ/2/ ድንግል ምስለ ሚካኤል/2/ ኧ□
ትርጉም፡- መልካሚቱ ማር□ም ድንግል ከሚካኤል □ር ነይ፡፡

## 42. የሥላሴን መንበር

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘው
ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት
አእላፋ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት/2/
የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እ□ሸበሸቡ □ሰማ□ መላእክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ
ይህን ልዩ ክብር ሊያዩ የታ□ሉ
በጽድቅ ሥራቸው ደምቀው ይታ□ሉ/2/
አዝ . . .
የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር
ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ/3/
አዝ . . .

## <u>43. እናመስግነው</u>

**/ተስፋዬ ኢዶ - ቁ.2/**

እናመስግነው/4/
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው/4/ ኧ□
ከኃጢአት ቀንበር ከሞት ቤት ለይቶ
መንግሥቱን የሰጠን ከሲኦል አውጥቶ
ዘለዓለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለኝ
መቼም የማይተወኝ ታላቅ አባት አለኝ
አዝ ....
ፍጡራን ቢንቁኝ መጎሰቆሌን አይተው
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋቢስ ነህ ብለው
እውነተኛው ረዳት አምላኬ መች ተወኝ
ሁለት እጄን ይዞ  ልጄ ተነስ አለኝ
አዝ ....
ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ላደለን
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን
ለታላቅ □ለታ□ ቴታ ለዋለልን
በእልልታ እንዘምር በአንድነት ሆነን
አዝ ....

## <u>44. ተነሱ እንዘምር</u>

ተነሱ እንዘምር/2/
በአንድነት ሆነን በእልልታ/2/ <u>ኧ□</u>/3/
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር/2/
ለኃ□ሉ ቴታ ለልወል እግዚአብሔር
አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል
አዝ . . .
ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተ ነህ
በሄድንበት ሁሉ ትከተለናለህ
ከእንቅፋት ከድንጋይ ትሰውረናለህ
አዝ . . .
ስለመልካም ሥራህ ለለብን ውለታ
ለማይነገረው የማዳን ስጦታህ
ተመስገን እንበልህ ከጧት እስከማታ
ሌላ ምንም የለን የምንከፍልህ ጌታ
አዝ . . .
አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው ብንጠራው

አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት የአንተ ሥራ የአንተ ልዕልና
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና
አዝ . . .
መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን እናውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እስከዘለዓለም ለስምህ እንዘምር
አዝ . . .

## 45.ሠለስቱ ደቂቅን

/ዲ.ን መገርሳ በቀለ - ቁ.2 /

ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት/2/
እኛንም አድነን/2/ ሊቀመላእክት
እኛንም አድነን/2/ ገብርኤል ሊቀመላእክት /2/
ቂርቆስ ኢየሉጣን ያወጣህ ከእሳት/2/
እኛንም አድነን/2/ ሊቀመላእክት
እኛንም አድነን/2/ ገብርኤል ሊቀመላእክት /2/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት/2/
እኛንም አድነን/2/ ሊቀመላእክት
እኛንም አድነን/2/ ገብርኤል ሊቀመላእክት /2/

## 46.ከመ ትባርከነ

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ/2/
ተዋነይ በጽድቅ/4/ ገብርኤል ሐመልማለ □ርቅ/2/
ትርጉም፡- በክቡር መስቀልህ ትባርከን ዘንድ ገብርኤል ሆይ በእውነት በረድኤት ተመላለስ።

## 47.ንሴብሖ ለእግዚአብሔር

ንሴብሖ/፪/ ለእግዚአብሔር/፪/
ስቡሐ ዘተሰብሐ/፩/
እናመስግነው/፪/ እግዚአብሔርን/፪/

## 48.ሠራዊተ መላእክቲሁ

ሠራዊተ/፪/ መላእክቲሁ/፪/
ኀ□ ለመድኃኔ ዓለም/፪/ ይቀውሙ/፩/
*ትርጉም፡- □መትኃኔ ዓለም የመላእክት ሠራዊት በፊቱ ይቆማሉ*

## 49.እመቤቴ ጥላ ከለላዬ

እመቤቴ ጥላ ከለላዬ ረዳቴ የገነት ሙሽራ/፪/
የገነት ሙሽራ/፫/ ማርያም የልዑል ማደሪያ/፪/

50. **ጽላት ዘሙሴ**

ጽላት ዘሙሴ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና/፪/
ጸናጽል ዘውስተ ልብሱ ለአሮን ካህን/፪/
*ትርጉም፡- የሙሴ ጽላት ጳጦስ የተባለች የሲና ዕፅ በካህን አሮን ልብስ*
*የነበረች ጸናጽል እርሷ ነች*

## 51.ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይእቲ/፪/ ማርያም/፪/
ሙዳየ መና ግሩም ሙዳየ መና/፪/
*ትርጉም፡- የቅዱሳን ክብር የመና ሙዳይ ማርያም አንቺ ነሽ*

## *52.መሐርኒ ድንግል*

*መሐርኒ ድንግል ወተሰሃልኒ በበዘመኑ/፪/*
*ለእመ መሐርክኒ/፫/ አንተ ዘይኴንነኒ መኑ*
*ኩናኔ ሥጋ ወነፍስ/፫/ ወልድኪ አኮኑ* /፪/
***ትርጉም፡-*** *ድንግል ሆይ ማሪኝ በየዘመኑ ተለመኝን አንቺ ከማርሽኝ የሚፈርድብኝስ ማነው በሥጋና በነፍስ የሚፈርድ ልጅሽ አይደለምን?*

## *53. ለምኚ ድንግል*

*(ዲ.ምንዳዬ ብርሃኑ ቁ.፪)*

*ለምኚ ድንግል ለምኚ/፪/*
*ለኃጥአን/፫/ አይደለም ለጻድቃን* /፪/

*ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ*

- » *አዛኝ ሩኅሩኅ ነሽ*
- » *የጌታዬ እናት*
- » *ጸጋን የተሞላሽ*
- » *የአምላክ ማደሪያ*
- » *ለምነሽ አስምሪኝ*
- » *አማናዊት ጽዮን*
- » *ከእኔ አትለይኝ*

*አዝ...*

*ለምኚ ሐዘንሽ ሐዘኔ*

- » *ለእኔ ይሁን ድንግል*
- » *የተንከራተትሽው*
- » *በሀገረ እስራኤል*

» ትእግስትሽን ሳየው
» ልቤ ይመሰጣል
» የሐዘን እንባ ጎርፍ
» ዐይኔን ይሞላዋል

አዝ...

ለምኚ በቀራንዮ አምባ
» በዚያ በፍቅር ቦታ
» በእግረ መስቀሉ ስር
» ከክርስቶስ ጌታ
» ለእኛ ተሰጥተሻል
» እናት እንድትሆኚን
» ልጆችሽ ነንና
» ምልጃሽ አይለየን

አዝ...

ለምኚ አንደበቴን ቴታ
» በምስጋና መላው
» ደስ ይበልሽ ብዬ
» እኔም ላመስግናት
» አንደበቴን ጌታ
» በምስጋና መላው
» ደስ ይበልሽ ብዬ
» እኔም ላመስግናት

## 54. ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት

ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት/፪/
አትመረመርም/፪/ እጅግ ጥልቅ ናት/፪/ ኧኸ
በሥጋዊ ጥበብ ለማወቅ ቢቃጣ
የእምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመጣ } /፪/
አንዳንዱ በክደህት/፪/ ፈጣሪውን አጣ/፪/ ኧኸ
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ } /፪/
እንመነው አንካደው አማኑኤል ቸር ነው/፪/ ኧኸ
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት } /፪/
እንመናት አንካዳት የአምላክ እናት ናት/፪/ ኧኸ